# የምርጫ 2013 የዕጩ ምዝገባ ሂደት እና ወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የተሰጠ መግለጫ

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)

# የምርጫ 2013 የዕጩ ምዝገባ ሂደት እና ወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የተሰጠ መግለጫ

## የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)

### በሀገራችን እየተበራከቱ የመጡ የደህንነት ስጋቶችን በተመለከተ

ሀገራችን ኢትዮጵያ ባለፉት ሶስት አስርት ዓመታት ስትከተል በኖረችው ዘርን ያማከለ ፖለቲካ ምክንያት በብዙ ምስቅልቅሎሽ ውስጥ ስታልፍ ቆይታለች። በእነዚህ ዓመታት ከገጠሙን አስከፊ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ችግሮች መካከል ዜጎች በብሄር ማንነታቸው ምክንያት እየደረሰባቸው ያለው አሰቃቂ የሆነ የጅምላ እና የተናጠል ግድያ በዋነኝነት ይጠቀሳል። ይህ ችግር በሁሉም የሃገሪቱ አካባቢዎች የሚገኙ ዜጎች ደህንነት ላይ ከፍተኛ ስጋት የጋረጠ ቢሆንም የዘር ፖለቲካ ተቋማዊ መልክ ተሰጥቶት እንዲቀጥል መደረጉ ችግሩ በቀላሉ እንዳይፈታ ጋሬጣ ሆኖ ቆይቷል። በሃሰት መረጃዎች እና በፈጠራ ታሪኮች በዜጎች መካከል ቅራኔ እና ጥላቻን በመዝራት ስልጣን ለማራዘም እና ከዜጎች ሰቆቃ ለማትረፍ ያለሙ ሃይሎች ከዚህ ብሔር አይደሉም፣ የታሪካዊ ጠላቶቻችን ርዝራዥ ናቸው ወዘተ በሚሉ ምክንያቶች ዜጎች ለአመታት ከኖሩባቸው ስፍራዎች ተነቅለው እንዲሄዱ ግፊቶችን ማድረግ፣ በፍርሃት ተይዘው አካባቢውን ለቀው ለስደት እንዲዳረጉ ከዛም ሲከፋ በአሰቃቂ መልኩ በጅምላ ግድያዎችን መፈፀም የተለመደ ሆኗል።

በተለይም ባለፉት ሶስት ዓመታት በቡራዩ፣ በሻሸመኔ፣ በአርሲ፣ በጉራፈርዳ፣ በመተከል እና አካባቢው፣ በምዕራብ ወለጋ፣ በኮንሶ እና ሌሎችም ቦታዎች ዜጎች በብሄር ማንነታቸው እና በእምነታቸው ምክንያት በግፍ ተገድለዋል። ለእነዚህ ግድያዎች እና የዘር ማጽዳት ወንጀሎች ህወሐት ዋነኛ ተጠያቂ እንደሆነ ሲነገር ቢቆይም ፤ ከሕወሐት መወገድ በኃላም አልተቋረጡም። ይህ ክፍተት በመንግስት ደረጃ ያለውን አቅም ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ሲሆን በተለያዩ አካባቢዎች በዜጎች ላይ ለሚፈጸሙ ወንጀሎች ተጠያቂ መሆን ያለባቸው አካላት አሁንም በነፃነት እየተንቀሳቀሱ እና እያደራጁ እንዳሉ ማሳያ ነው።

ይህ አልበቃ ብሎ በሀገራችን ዜጎች የተረጋጋ ህይወት መምራት የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር ባለመቻላችን በውስጥ ያሉብንን ዘርፈ ብዙ ችግሮች ሸሽተ ወደ ስደት የሚሄዱ ወገኖቻችንን ሞት መስማት ዳግም ልብ ይሰብራል። በያዝነው ሳምንት በየመን ሰንዐ እስር ቤት ውስጥ በተነሳ የእሳት ቃጠሎ ህይወታቸውን ያጡ ዜጎቻችን ሞት መስማታችን ክፉኛ አሳዝኖናል።

በትግራይ ክልል ያለው አሳሳቢ የሰብአዊ ቀውስ እና የሰብአዊ መብት ጥሰት አስፈላጊው ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። ኢትዮጵያውያን፣ መንግስት እና አለም አቀፍ ድርጅቶች የዜጎችን ህይወት ለመታደግ የሚያደርጉት ርብርብ ተጠናክሮ እንዲቀጥል እያስታወስን በክልሉ የተከሰተውን ከፍተኛ የሆነ የውሃ ፣ የምግብ፣ የመድሀኒት እና የህክምና አገልግሎት እጥረት ለመቅረፍ የሚሰሩ የእርዳታ ድርጅቶች መንግስት አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርግ እንጠይቃለን።

በሃገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች የተፈፀሙ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን መሪነት ፤ ከመንግሰት እና ከአለም አቀፍ ሰብአዊ ድርጅቶች የቁስ እና የሙያ ድጋፍ እየተደረገለት የማጣራት ስራ እንዲሰራ፤ አጥፊዎችም ለህግ እንዲቀርቡ እና የተጎጂዎች እንባ እንዲታበስ እንጠይቃልን።

ዜጎች በሰቆቃ እንዲኖሩ የሚያደርጉ የታጠቁ ሃይሎች እና የዜጎችን ደህንነት መጠበቅ ተቀዳሚ ዓላማቸው መሆን ሲገባው ከአሰቃቂ ግድያዎች ሊታደጓቸው ያልቻሉ የደህንነት ተቋማት የዜጎችን ህይወት እና ደህንነት ለመጠበቅ ባለመቻላቸው ሊጠየቁ ይገባል።

የዜጎች መፈናቀል፣ መገደል እና ሌሎች የሰብዓዊ መብተ ጥሰቶች ከመደጋገማቸው የተነሳ እየተለመዱ መምጣታቸው ትኩረት እንዲያጡ ከማድረጉም በላይ ከቀን ወደ ቀን ልንገነባው ከምንፈልገው በአብሮነት የተሳሰረ ማሕበረሰብ እያራቀን መምጣቱ የማይቀር ነው።

ኢትዮጵያውን በሀገራችን በፈቀድነው ቦታ በነፃነት መኖር እንድንችል መንግስት ያለበትን ሀገርን የመምራት እና ዜጎች በተፈጥሮ ያገኙትን በሕይወት የመኖር መብት የማስጠበቅ ኃላፊነቱን እንዲወጣ አበክረን ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

ኢዜማ በሃገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች ያሉ ዜጎቻችን ደህንነት አሁንም ከምንም በላይ ቅድምያ ተሰጥቶት ሊሰራ የሚገባ መሆኑን ያምናል፣ ስለሆነም ዛሬም የዜጎችን የጋራ ደህንነት ለማስጠበቅ ሃላፊነቱ እና አቅሙ ያለው መንግስት ሁነኛና የማያዳግም እርመጃ ወስዶ የዜጎችን ደህንነት በማስጠበቅ ያለውን ቁርጥኝነት እንዲያሳይ እንጠይቃለን።

## የእጩ ምዝገባ ሒደት እና ያጋጠሙ ችግሮች

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በ2013 ዓ.ም ምርጫ በዘጠኝ ክልሎች እና በሁለት ከተማ አስተዳደሮች ለመወዳደር እጩዎችን አዘጋጅቷል።

በ406 የምርጫ ክልሎች ላይ የወረዳው አባላት ጠቅላላ ጉባኤ ተጠርቶ በአመልካች እጨዎች መካከል በተደረገ ፋክክር እጩዎችን ማስመረጣችን ይታወሳል፡፡ ለዚህም በአካባቢዉ ማህበረሰብ ዘንድ ያለ ተቀባይነት፤ የትምህርት ደረጃቸዉ፣ የስራ ልምዳቸዉ፣ እና የግል ስብዕናቸዉ በዋናነት ለዕጩ መመልመያ መስፈርትነት በማገልገል ዕጩዎች ተመርጠዋል፡፡

ኢዜማ በመላ ሀገሪቱ ለተመረጡት እጩዎች ከየካቲት 1 እስከ 7 ባሉት ቀናት የአንድ ቀን ስልጠና ተሰጥቶ ለምዝገባ ዝግጅት ቢያደርግም እንደ ታሰበው በጥቂት ቀናት እጩዎችን አስመዝግቦ መጨረስ አልቻለም፡፡ ምርጫ ቦርድ ባወጣው የግዜ ሰሌዳ መሰረት ከየካቲት 8 ቀን 2013 ዓ.ም አንስቶ ምዝገባ በጀመረባቸው ስፍራዎች ሁሉ ኢዜማ እጩዎቹን እያስመዘገበ ቆይቷል፡፡ ምርጫ ቦርድ የካቲት 30 2013 ዓ.ም. ምዝገባ መጠናቀቁን ገልፆ ፤ በምርጫ ወረዳ ደረጃ ችግር ያለባቸውን ቦታዎች ብቻ የሚያይ መሆኑን አስታውቋል፡፡ በዚህ መግለጫ ኢዜማ እጩዎችን በማስመዝገብ ሂደት የገጠሙትን በፍጥነት ሊፈቱ የሚገባቸውን እና ለመራጮች ምዝገባ ትምህርት ሊወስድባቸው የሚገቡትን ችግሮችን በመለየት ማሳወቅ ተገቢ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

1. ከምርጫ ቦርድ ጋር በተያያዘ የገጠሙን ችግሮች

ምንም እንኳን አብዛኛው የምርጫ ቦርድ ኃላፊዎች በማዕከልም ሆነ በየምርጫ ወረዳው በቅንነት፤ በገለልተኛነት እና በችግር ፈቺነት መልካም የሚባል አፈፃፀም ያሳዩና አጋጥመውን የነበሩ ችግሮችን በአመዛኙ ለመፍታት የቻሉ ቢሆንም፤ በምርጫ ቦርድ በኩል የታዩ ክፍተቶችን ለማቅረብ ያህል

ሀ. <u>የምርጫ ቦርድ የወረዳ ቢሮዎችን በግዜ ሰሌዳ መሰረት አለመክፈት</u>

የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ እጩዎች ምዝገባ የካቲት 8 2013 ይጀመራል የሚል ሰሌዳ ያወጣ ቢሆንም በአብዛኛው የምርጫ ወረዳዎች ተከፍተዉ አገልግሎት መስጠት የቻሉት ከተቀመጠላቸዉ የጊዜ ሰለዳ ዘግይተው ነበር፡፡ የምርጫ ቦርድ የምርጫ ክልል ቢሮዎች በተያዘላቸዉ ጊዜ ያለመከፈታቸዉ ችግር በዘጠኙም ክልሎች እና በሁለቱም ከተማ አስተዳደሮች የገጠመ ችግር ቢሆንም ተዘግተዉ የቆዩትን ቢሮዎች በዘገዩት ጊዜ ያህል በቂ የማካካሻ ጊዜ አልተሰጣቸውም፡፡ ለምሳሌ ምዕራብ ሸዋ፤ ሰሜን ሸዋ ፤ጉጂ፤ ጅማ፤ አፋር እና በሱማሌ ክልል ከአስር እስከ አስራ

አራት ቀን ተዘግተው የተከፈቱ የምርጫ ክልል ቢሮዎች ክፍት ሆነው አገልግሎት የሰጡት ከሁለት እስከ አራት ቀን ነው።

ለ. <u>ከህግ፣ ደንብ እና መመሪያ ውጪ እንዲሚሉ የሚጠየቁ ጥያቄዎች</u>

- ✓ የመንግስት ሠራተኞች የለቀቁበትን ማስረጃ መጠየቅ፣
- ✓ ከምርጫ ክልሉ ውጪ የሚኖሩ እጩዎች በምርጫ ወረዳው መወለዳቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ይዘው ቢቀርቡም ከመመሪው ውጪ ምዝገባ መከልከል
- ✓ በእጩነት ለመመዝገብ የተለያዩ ህጋዊ ሰነዶችን ማቅረብ ህጉ ቢፈቅድም ከቀበሌ መታወቂያ ውጪ አንቀበልም ማለት
- ✓ ከመመሪያው ውጪ እንዲሚሉ በሚጠየቁ ሰነዶች ምክኒያት ዕጩዎች የተለያየ እንግልት ደርሶባቸዋል

ሐ. **<u>የምርጫ ቦርድ የምርጫ ክልል ቢሮ የተመደቡ የምርጫ አስፈጻሚዎች ወይም እጩ መዝጋቢዎች አቅም እና ብቃት ዉስንነት</u>**

- ✓ የምርጫ አስፈጻሚዎች ወይም መዝጋቢዎች የአቅም ውስንነት፣ የምዝገባ ስርዓቱን እና ቴክኖሎጂውን አለመላመድ
- ✓ የመመዝገቢያ ሰዓቱ በመደበኛ የስራ ሰዓት ሆኖ ሳለ ቢሮ ቆልፎ የመጥፋት ችግር ወይም ዋና መዝጋቢዎች ወይም የቴክኖሎጂ ባለሙያዎች ከስራ ገበታቸዉ መሰወር በብዙ ቦታዎች በተደጋጋሚ ታይቷል
- ✓ ለምዝገባ የሚወስደው ጊዜ በምርጫ ክልል ቢሮዎች መሀል ሰፊ ልዩነት የነበራቸዉ ሲሆን አንዳንድ ቢሮዎች እጩ ለመመዝገብ ሰዐታት ይወስዱ ነበር

መ. በተወሰኑ አካባቢዎች የምርጫ ቦርድ የምርጫ ክልል ቢሮዎች በእጩነት የሚመዘገቡ አካል ጉዳተኞችን ከግምት ያላስገባ ነበር። በተለይ በከተማ ላይ የተከፈቱ ቢሮዎች አንዳንዶቹ አራተኛ እና አምስተኛ ፎቅ ላይ የተከፈቱ ሲሆን አካል ጉዳተኞች ለምዝገባ ሲመጡም ለችግር እና እንግልት ተዳርገዋል።

## 2. <u>ከመንግስት ጋር በተያያዘ የገጠሙ ችግሮች</u>

- ✓ ኢዜማ በኦሮምያ ውስጥ ባሉ ምርጫ ወረዳዎች ባቀረባቸዉ እጩዎች ላይ ከመመዝገባቸዉ በፊት ዛቻ እና ማስፈራራት
- ✓ የፀጥታ ሁኔታ እጩ ለማስመዝገብ የማይቻልበት ቦታዎች መኖር
- ✓ በተለያዩ አካባቢዎች የኢዜማ እጩዎች ከተመዘገቡ በኋላ እንዲሰርዙ ወይም ራሳቸዉ እንዲያገሉ ማስፈራራት
- ✓ ዕጩዎችን ከተመዘገቡ በኋላ ያለመከሰስ ሙሉ መብት እንዳላቸው እየታወቀ ማሰር፣ መደብደብ

ከላይ የተጠቀሱ ችግሮች ቢኖሩም በሁሉም ክልሎች እና ከተማ መስተዳድሮች ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ለክልል ምክር ቤት እጩዎችን አስመዝግበናል። በሱማሌ በኦሮሚያና በቤንሻንጉል በምርጫ ክልል ቢሮዎች በአግባቡ ያለመከፈት ችግር እና ከፀጥታ ጋር በተያያዙ ምክንያቶች ያዘጋጀናቸውን እጩዎች በከፊል ማስመዝገብ አልቻልንም። በጋምቤላ አኮቦ እና በአፋር አባላ የሚባሉ ምርጫ ክልሎች ምርጫ ቦርድ ቢሮ እንደከፈተ ሪፓርት ቢያደርግም በክልሉ ያለን መዋቅር አመራር፣ አባላት እንዲሁም እጩዎች የምርጫ ክልል ቢሮዎቹን ሊያገኙዋቸው አልቻሉም። በሲዳማ ክልል በሦስት ምርጫ ክልሎች በመዝጋቢ በተፈጠረ ችግር አባላት ሊመዘገቡ አልቻሉም፣ በኦሮሚያ ክልል በበርካታ የምርጫ ክልሎች ቢሮ ባለመከፈት፣ በፀጥታ ችግር፣ በመዝጋቢ ተባባሪ አለመሆን ምክኒያት በርካታ ዕጩዎቻችንን ማስመዝገብ አልቻልንም። በተመሳሳይ በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል በፀጥታ ችግር ምክኒያት በርካታ ዕጩዎቻችንን ማስመዝገብ አልቻልንም።

ከምርጫ ክልል ቢሮዎች ጋር በተያያዘ የገጠሙንን ችግሮች ካዘጋጀናቸው እጩዎች ስም ዝርዝር እና የምርጫ ክልል ስም ጋር በማያያዝ ለምርጫ ቦርድ የምናሳውቅ ሲሆን በፀጥታ ችግር ምክንያት እጩዎችን ለማስመዝገብ ያልቻልንባቸው ቦታዎች ላይ በአጃቢ እጩዎችን ለማስመዝገብ ያደረግነው ጥረት አልተሳካም።

### በምርጫ ቦርድና በመንግስት ሊወሰዱ የሚገቡ የመፍትሄ ሀሳቦች

1. መንግስት በምስራቅ ወለጋ እና በምዕራብ ወለጋ እንዲሁም በቤንሻንጉል ክልል ምርጫን ለማካሄድ የሚያስችል የፀጥታ ሁኔታ መፈጠር አለበት። ከዚህም በተጨማሪ በየክልሉ ላሉ ካድሬዎች እና የፀጥታ መዋቅር ላለፉት አምስት የይስሙላ ምርጫዎች ሲያደርጉ እንደነበሩት የተፎካካሪ ፓርቲ ተወዳዳሪዎችን ከማዋከብ እና ከማስፈራራት እንዲቆጠቡ በይፋ ትዕዛዝ እንዲሰጥልን እንጠይቃለን።

2. ምርጫ ቦርድ ላለበት የአቅም ውስንነት በተለይ የክልል መንግስታት የቢሮ እና ተያያዥ ችግሮች በማመቻቸት ረገድ የማይተካ ሚና ያላቸው በመሆኑ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት በፍጥነት የሚተገበሩት ስራ እንዲያደርጉት መመሪያ እንዲተላለፍ እንጠይቃለን፡፡
3. ምርጫ ቦርድ የፀጥታ ችግር ያለባቸውን ቦታዎቸ እና በጣብያዎች በቂ የመመዝገቢያ ግዜ ባለመሰጠቱ እንዲሁም አሁን ድረስ ሊገኙ ባልቻሉት የምርጫ ክልልሎች ባቀረብናው ዝርዝር መሰረት ዕጩዎቻችንን በማዕከል እንዲመዘግብልን እንጠይቃለን፡፡
4. የመራጮች ምዝገባ ከእጩዎች ምዝገባ አንፃር የሚያስፈልገው የቢሮ ብዛት እና የቁሳቁስ ማጓጓዝ ሰፊ በመሆኑ መጪውን ሀገራዊ ምርጫ የተሳካ ለማድረግ መሟላት ያለባቸው ግብአቶች በአስቸኳይ እንዲሟሉ እንጠይቃለን፡፡
5. የመዝጋቢዎች ብቃት እና መመርያን ተከትሎ መስራት ለመራጮች ምዝገባ በከፍተኛ ሁኔታ ሊሻሻል የሚገባዉ ነዉ ብለን እናምናለን፡፡ አሁን በዕጩዎች ምዝገባ የታዩ ጉድለቶች በአፋጣኝ የዕርምት እርምጃ ካልተወሰደባቸው የመራጮች የምዝገባ ሂደት ላይ ችግር እንዳያጋጥም ስጋት አለን፡፡ ለዚህም ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የእርምት እርምጃ እንዲወስድ እንጠይቃለን፡፡

ንቁ ዜጋ! ምቹ ሀገር!

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)

መጋቢት 3 ቀን 2013 ዓ.ም

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ